# ጠላት ወዳጅ ላይሆን መለማመጥ ውርደት!

ሰሞኑን የወያኔ አገዛዝ የፖለቲካ እስረኞችን ምሕረት ጠይቁ፤ አጥፍተናል ብላችሁ ፈርሙ፤ ተለማመጡን እያሉ ጫና በማድረግ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ይህ ከሀዲ አገዛዝ ሳውዲ አረብያ በዜጎች ላይ የምታደርሰውን ግፍ በመቃወም ሰልፍ የሞከሩትን ቀጥቅጦ ሲያስር፣ በሳውዲ ያለውም የወያኔ አምባሳደር ዜጎቻችን አጥፍተዋልና ይቅርታ አድርጉልን ሲል በግፍ ላይ ቅሌትና ውርደት ጨምሮበታል። ከወያኔ የሚገኝ ምህረት የለም -- ውርደትና ቅሌት እንጂ።

ወያኔ ገና ስልጣን ከመያዙ ባሕታዊውን ሳይቀር አጠፋሁ ብላችሁ ፈርሙ ሲል እንደነበረ ይታወሳል። ይህ ድርጊት በተለይ ሟቹን አምባገነን ያስደስተው የነበር መሆኑ ይታወቃል። ግብዝና የዝቅተኛነት ስሜት የሚያጠቃው ነበርና ሰውን ያዋረደ ሲመስለው ይረካ እንደነበር በቅርብ ይህን ቡከን ፍጡር የሚያውቁት ሁሉ ይናገራሉ። እስረኞች /ተቃዋሚዎች ለመኑኝ፤ ተንበረከኩ በሚል ሞራል ያደቀቀና ሌሎችንም ተስፋ ያስቆረጠ ይመስለዋል። ለዚህም ነው ቅጥረኞቹ በሆኑ ፕሮፌሰሮችና ፓስተሮች ተደግፎ የፖለቲካ እስረኞችን ምሕረት ካልጠየቃችሁ መከራችሁ ይበዛል፤ ወደ ዝዋይ ትጋዛላችሁ፤ ሞትም ሊመጣ ይችላል በሚል ያስፈራራል ያስጨንቃል። መሰል ጫና አሁንም በፖለቲካ እስረኞች ላይ ተጀምሯል። ለዚህ ተሸናፊ መሆን ደግሞ ከእስር ሊያስወጣ ቢችልም ህሊናንና ስብዕናንም ይነጥቃል፤ ያዋርዳል፤ አሊያም ተስፋ ያስቆርጣል። ወግድ እምቢ ያሉት ደግሞ በዚያው ልክ የሚከበሩና በህዝብም የሚወደዱ ናቸው።

ጠላትን መለማመጥ ወይም ለጠላት መጎንበስ ትርፉ ውርደትና ውድቀት ለመሆኑ በታሪካችን ያየነው ነው። በርግጥ በአጼው ዘመን ባንዶች ለሹመት ቢበቁም የታሪክ ትቢያ መሆናቸውን ግን አርበኞችን ያሞገሰው ትውልድ አልረሳም። ውርደት ነበር ካባቸው። በጣሊያን ፊታውራሪና ደጃዝማች የተባሉትም -- የመለስ ዜናዊ አያትንም ጨምሮ -- ቅሌትን እንደተከናነቡ ሁሉም የሚያውቀው ነው። እስከዛሬም ባንዳ

በአማርኛችን ቡድን ማለት ሳይሆን ከሀዲና ወራዳ ማለት ነው። ገዢዎች ሕዝብን በቀቢጸ ተስፋ ጉድጓድ መክተት አላማቸውና ተልዕኮአቸው ነው። ሕዝብን ተስፋ ካስቆረጡ የመቃወም ወኔውን ያጣል። አገዛዞች ወደ ቀቢጸ ተስፋ ሕዝብን የሚከቱት በአፈና፣ በአልባሌ ባሕሎች ከጥቅም ውጪ በማድረግ፣ አይበገሬ ነን በሚል ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ በማናወዝ፣ ስብዕና አሳጥተው በጥቅም በመግዛትም ጭምር ነው። ቀቢጸ ተስፋ ጨለምተኝትን ይወልዳል ወይም ተወራራሾች ናቸው። አበቃልን፣ ገና ሳይዋጉ ተሸነፍን ማለትን፣ ሰበ ሰብ ፈጥሮ ከትግል መራቅን፣ ለአገዛዝ ጸጥ ለጥ ብሎ መገዛትን ያመጣል።

ትግሉ እየተራዘመ ሲመጣ፣ ቀቢጸ ተስፋ ቤቱን ባንጎላችን ውስጥ ሲሰራ ወደ ጠላት ሊኖረን የሚገባውም እይታ መለወጥ ይጀምራል። ጠላት ወዳጅ መስሎ ይታየናል ወይም ጠላትን ጠላት አለማለቱና ለመተቃቀፍ መጣሩን ያስከጅለናል። ቆሞ መታገል ቀርቶ ተንበርክኮ ልመና የሚያዋጣው መንገድ ና የሰለጠነ ፖለቲካ ሆኖ ይመጣብናል። በዚህ መልክ በየጊዜው አንጃ ብቅ ብቅ ያለባቸው ድርጅቶች በቂ ተመክሮ ያላቸው ሲሆን በሰሞኑ በ ኢ.ሕ.አ.ፓ ይፋ የሆነው የሚቹ ብርሃነ መስቀል ረዳ ለፖሊስ የሰጠው ቃል ሰነድ በቂ ምስክር ነው። ግለሰቡ ወደ አንጃነት የነጎደውና ደርግንም ወዳጅና አብዮታዊ ብሎ ለመውሰድ የተነሳው በነበረው የሥልጣን ጥም በመነሳት ነው። ስልጣን ለግል ፍሊጋ የሚያብከነንክናቸው ሰዎች ሳይውል ሳይድር ከሆነላቸው አምባገነን ከከሸፈ ደግሞ አንጃ እንደሚሆኑ በግለሰቡም ሆነ በመሰሎቹ እስከዛሬ ሲታይ የቆየ ነው። ይህ ያፈቀረው ደርግ አንቆ የገደለው አንጃ ድርጅቱን ሊከዳና ሊጎዳ ሲዳዳው ወዲያውኑ በተወሰኑ የአመራር አባሎች ላይ መዝመትና ክሊክ የሚል ቅጽል ሰጦ ማጥቃት ጀመረ። ይህ ደግሞ እስከዛሬም የአንጃዎች ሁሉ መለያ ሆኖ የሚታይ ነው። ብርሃነ መስቀል የድርጅቱን ስም ባይሰርቅም ድርጅቱን በሚጎዱ ስምሪቶች ላይ ተገኝቷል። ከደርግ ጋር ማበርና መስራት አለብን ያለውና ሌላው መሪ የነበረ የአንጃ አባል የተካፈለውን አቅዋም ለአባላት ቀርቦ ውድቅ ከሆነ በኋላና ወደደርግ ለመጠጋት ያደረገው ሙከራና ልመና ሰሚ እንዲያጣ ከተደረገ

በኋላ ሸሽቶ በሰነዱ ወደተጠቀሱት የሸዋ አካባቢዎች ሄደ። በሰነዱ እንደገለጸው ግን ደርግን ሊታገል ሳይሆን በዚያም ሆኖ ልምጥምጡን ለመቀጠል ነበር። እምነቱ የደርብ ፕሮግራም ትክክል ነው፤ ድደርግ ተራማጅና አብዮታዊ ነው፤ ኢሕአፓ በሶስት መሪዎች ሙሉ ቁጥትር ስር ወድቆ አድሃሪ ሆኗል ወዘተ የሚል ነበር። ዛሬ ወዳጁ ነበርኩ የምትል ሴት ይህን መሪ አንጃ ከቶም አልነበረም ያለችውንም ብርሃነ መስቀል በዚህ ለፖሊስ በሰጠው ቃል ያስተባብለዋል። አዋቂ ነን ብለው ቢሆንም ሆነ ብርሃነ መስቀል አንጃ አልሆነም፤ ደርግንም አልደገፈም ብለው ድርጅቱን ሊኮንኑ የሞከሩትን ሁሉ በቃሉ ያሳፍራቸዋል። አንጃዎች ድርጅት ሊያጠቁ ሲነሱ --ካለው አገዛዝ ጋር መተቃቀፍ ይፈልጋሉና-- በቅድሚያ ድርጅቱ ተበላሽቷል፤ ደክሟል፤ ለሕዝብ ተነጥሏል፤ ልሳኑ ወይም ጽሁፎቹ የተሳሳቱ ናቸው፤ ስድብ አዘል ብቻ ናቸው ወዘተ በሚል የቀቢጸ ተስፋ ጫጫታ ተሰማርተው ነበር፤ ቀጣዮቹም የተለየ ሲሉ አልሰማንም። ድርጅቱን ኮነኑ፤ የደርግ ጠቋሚና ገራፊ ሆነው የድርጅት አባላትና ደጋፊዎችን ጎዱ፤ ድርጅቱንና ትግልን አጠቁ። ቀደም ብለን እንዳልነው ቀጣይ አንጃዎችም የተለየ አላደረጉም -- ብርሃን መስቀልና ጓደኞቹ በቀደዱት የክህደት ቦይ ነው የፈሰሱት፤ ፈሰውም ያሉት። የመጀመሪያው አንጃ መሪ ደርግና መሪው ፋሺስት ኮለኔል አብዮታዊና ዴምክራሲያዊ ናቸው ብሎ መለማመጥ እንደሞከረው ሁሉ ሌላው ቆይቶ የመጣው አንጃ ደግሞ ለወያኔ ሕገ መንግስት ያልከውን እንቀበላለን፤ ብረት መቼም አናነሳም፤ ህጋዊነት ተሰጥቶን በሰላም መታገል እንፈልጋለን ብለን ሰነድ እንፈርም ያሉትን አቅዋማቸውን ለአባላት ሁሉ እንዲተላለፍ ተደርጎ ውድቅ ሲሆን ያው ወደ አንጃነቱ ተጓዙ። ስለ ሀገር ቤቱ መዋቅር ለማወቅ የጣሩትም በጊዜ ስለከሸፈባቸው ማጋለጥ ባይችሉም የድርጅቱን ምስጢር ግን ባለ አቅማቸው ይፋ አድርገዋል። እነዚህም እንደበፊቶቹ በሁለት አመራር አባላት ላይ ጻያፍ ዘመቻ አካሂደዋል። የቀድሞዎቹ ከሀዲዎች እንዳደረጉት ሁሉ ድርጅቱ ደክሟል፤ ከድርጅቶችና ከህዝብ ተነጥሏል፤ የሚጽፈው ሁሉ ትችት ሳይሆን ስድብ ነው፤ የወያኔን የበላይነት ተቀብሎ ባለመታገሉ ጫጭቷል ወዘተ ብለው ጮሁ። ድርጅቱን የሚጠሉ ሁሉ ሀይ ሀይ በርቱ አሏቸው -- ግን የደርጅት

ስም ሳይቀር ቢሰርቁም ከውድቀታቸው አልዳኑም። ወያኔን ለመለማመጥና ማሪኝ አብዮቴን በማረን ወያኔ ለመተካት ስብዕና አጥተው ሲርመጠመጡ ወያኔ ያሰራቸውን ጓዶቻችንን ይፍታ ብለን ከወዲሁም አናስጭንቀውም አንጠይቀውም እስከማለትም ደርሰው ነበር። መለስን አንቱ በሉት፡ ወያኔ ሳይህን ኢሕአዴግ ይባል ብለውም ነበር። እንደ ብርሃነ መስቀሉ ኑዛዜ የነዚህም በወረቀት ሆነ በቴፕ ቅጂ ደረጃ በመረጃነት ያለ ነው፡፡ ወያኔም በእጁ ሳላልገቡ አልገረፋቸውም እንጂ ባሉበት ባዕድ ሀገር ወግዱ ከዚያው ብሏቸው እነሆ ከስመዋል -- አዲስ አንጃ ወልደው ሊያሳድጉና ሊያድጉ የጣሩትም -- ስልቱ ያው ቢሆንም (የተወሰኑ መሪዎችን መወንጀል፤ ደክመናል ጫጭተናል ማለት፤ የድርጅቱን ጽሁፍ ሆነ ራዲዮ ማክቸልቸል፤ ለጠላት መሳሪያ መሆን ወዘተ) -- ከሽፏል።

ጠላት ወዳጅ ላይሆን መለማመጥ ውርደት ነው ትርፉ። ጠላት ልቀፋችሁ ቢልም ስብዕና ገፎ ከሕዝብም አጣልቶ ነው። ደርግን ማሪኝ አብዮቴ ብለው ገብተው ጓዶቻቸው ላይ የጠቆሙና ስየልም የፈጸሙትን ውሎ አድሮ በልቷቸዋል። ከወያኔም ተቃቅፈን ያሉት ስንቶቹም ተበልተዋል፤ ደብዛቸው ጠፍቷል፤ ወይም በስካርና በአደንዛዥ ዕጽ እንዲደነዝዙ ተደርገዋል። ክህደት ውርደት ነው፤ አቅፈውት ሲተኑ ቀስቃሽና ወንጃይም ነው። ትግልን የሚያውቁ ሁሉ ትግል መራራና ከባድ መሆኑን ይረዳሉ። ለፈጣም ድልና ለግል ስልጣን ወይም ጥቅም ወደ ትግል ዘው ያሉት ደግሞ ጊዜው ሲራዘም ወደ ተስፋ መቁረጡ ያመሩና ሁሉም ጨልሞባቸው ለጠላት መስገዱን ይመርጣሉ።  በርግጥ አንዳንዶች ወደ ድርጅት የሚገቡት በየታሪክ ማጠፊያ ላይ ደግመው ደጋመው አንጃ ለመሆን ወይም ከድርጅት ድርጅት እንደ ፌንጣ ለመዝለል ነውን ብሎ መጠየቅን የግድ ያደርጋሉ። ጊዜ መርዘሙ ግን ትግልን ሊያስተው የሚችል መሆን የለበትም ነበር። በትግል የቆዩ ድርጅቶችንም አረጁ በቃቸው ያብቁ ብሎ መተቸት አላዋቂነት ነው። እንደምሳሌ ብንውስድ የደቡብ አፍሪካው ዛሬ መሪ የሆነው አፍሪካ ብሔራዊ ኮንግሬስ የተቋቋመው በአውሮጳ አቆጣጠር በ 1912 ሲሆን ለስልጣን የበቃው በ 1975 ዓ.ም. ነው። ጸንቶ

ትግልን መቀጠል የሚመሰገን መሆኑን በዘንድሮአችን በተመሰረቱ ማግስት ከ እሳት ራት ባነሰ ዕድሜ ብዙ ቡድኖችና ድርጅቶች ሲጠፉ ማየታችን የሚያስተምረን። ለዚህም ነው ለጠላት የሚያመች ተስፋ መቁረጥና ጨለምተኛነትን መታገል ማቸነፍ ያለብን። ካልሆነ ያው ለጠላት መጎንበስ ተከታይ ይሆናል። የፖለቲካ ትግል ለስልጣን ነው ቢባልም ለሕዝብ ስልጣን ነውና እኔ ለስልጣን አልበቃሁም ብሎ፤ ሽንፈት ደረሰብን ብሎ  ተስፋ ቆርጦ ለጠላት መጎንበስ ከስህተት ያለፈ ከባድ ጥፋት ነው።

ፈረንጆች ነገር ከጨነቀ ጠጣር ዓይነት ሲሆን ወይ ተበደር ወይ ለምን፤ አሊያም ስረቅ የሚል አባባል አላቸው። የ እኛው ገሞራው ደግሞ "ያሰብከው አላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ ሁናቴው ሲጠጥር/ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር!" ብሎ ጨርሶታል። ያሰብከው ዓላማ አልሞላ ብሎ ሁኔታው ሲጠጥር እጅህን ስጥና ሆድህን አስቀድም አልተባለም። በዓላማቸው ጸንተው ለዓመታት የታገሉት -- ራሱን ገሞራውን ጨምሮ -- ለጽናት ምስክሮች ናቸው። ወይኔ ጉዴ ፈላ፤ ተሸነፍን፤ ሁናቴው ጠጠረ ወዘተ ብለው ደረት ድለቃና ኡኡታ ውስጥ አልተዘፈቁም። ይባስ ብለውም በትግሉና በታጋይ ድርጅቶች ላይም ተነስተው ክፍፍልና ቀቢጸ ተስፋን ሊያሰፍኑ አልጣሩም። በአጭሩ አንጃ አልሆኑም ወይም ሊሆኑ አልዳዳቸውም። ይህን ነው መገንዘብና ሀቅ ብለን መቀበል ያለብን። ጠላትን ማመን ወይም መለማመጥ ብዙዉን ጊዜ ጥሩ ውጤት የለውም -- አረመኔነታቸውን አይቀይሩምና። መንግስቱ ሀይለማርያም ወደ ጅቡቲ የሸሸውን ሚቹን ዶክተር እሸቱ ጮሌን በስልክ ተመለስ አይዞህ ብሎ ደልሎ ሲመለስ ለረጅም እስር ዳርጎታል። ለሻለቃ ሞገስ ጓድህ ነኝ ብከዳህ ልሙት ብሎ አደናግሮ ያው ገድሎታል። ምሳሌዎች ብዙ ናቸው -- ወያኔም አባባሎ ግን ሲያምኑት የፈጃቸው ጥቂት አይደሉም። ቀደም ታሪክ ብለን ከሄድን ደግሞ በኮንጎ ለምሳሌ ምሕረት አውጃለሁ ብሎ ሚቹ ሞቡቱ ተናግሮ ተቀብለው የገቡትን እነ ፒየር ሙለሌ ዓይነቶቹን የአፍሪካ ጀግኖች በአደባባይ ስቅሏቸዋል። በርበሬ አይሆን ዕጣን ተብሏል። ጽናትና ብቃት ያላቸውን መሪዎችና ድርጅቶች እንደግፍ።

**ወያኔ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ሁሉ ጠላት ነው!**

**ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም፣ ይቀጥል !!**